የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ኤምባሲ ስቶክሆልም
Embassy of the Federal
Democratic Republic of Ethiopia
Stockholm

ቀን 06/08/2020
Date
ቁጥር-----------------------------
Ref. No.

# ማስታወቂያ

## ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ድጋፍ ለማድረግ ለምትፈልጉ ሁሉ፡

የሁሉም ኢትዮጵያዊያን አሻራ ያረፈበት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በአሁኑ ጊዜ የመጀመሪያ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት ተጠናቆ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ደርሷል። የግድቡ ቀጣይ የግንባታ ስራ እስኪጠናቀቅ ድረስ የኢትዮጵያዊያን ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚያስፈልገው በመሆኑ በአገር ውስጥም ሆነ ውጭ የሚገኙ ዜጎች ቦንድ በመግዛት፣ ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት፣ የኢትዮጵያን አቋም በአለም አቀፍ መድረክ በማንጸባረቅ እና በሌሎችም መንገዶች ድጋፍ በማድረግ የሚያስመሰግን ስራ እየሰሩ ይገኛሉ። በመሆኑም በኖርዲክ አገራት ማለትም በስዊድን፣ ኖርዌ፣ ዴንማርክ እና ፊንላንድ የምትገኙ እና የህዳሴ ግድብ ቦንድ ለመግዛት እና የገንዘብ ስጦታ ለማበርከት የምትፈልጉ ኢትዮጵያዊያን ከዚህ ቀጥሎ የተቀመጡትን የባንክ አካውንቶች መጠቀም የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን ድጋፋችሁን ስትልኩ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ እንድታስገቡ እናሳስባለን።

- ቦንድ መግዛት የሚቻለው በአሜሪካ ዶላር፣ በዩሮ እና በብሪትሽ ፓውንድ ብቻ ነው፣
- በስጦታ መልክ ለመበርከት የአራቱንም አገራት ገንዘብ መጠቀም ይቻላል፣
- ቦንድ በአካል ወይንም በባንክ በኩል መግዛት ይቻላል፣ በባንክ የሚልኩ ከሆነ ከታች የተቀመጡትን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንቶች ይጠቀሙ፣ በአካል ከሆነ በካሽ ይዘው መምጣት ያስፈልጋል፣
- ወደ ንግድ ባንክ ከላኩ በኋላ የላኩበትን ደረሰኝ፣ ከአንድ ጉርድ ፎቶግራፍ እና ፓስፖርት/ትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ቅጂ ጋር ወደ ኤምባሲው በፖስታ ይላኩ፣ ኤምባሲው ደረሰኙን ከተቀበለ በኋላ የቦንድ ሰርትፊኬቱን ወደ አድራሻዎ ይልካል፣
- በስጦታ የሚያበረክቱ ከሆነ በአካል በመገኘት ወይንም ከታች ወደ ተጠቀሰው የኤምባሲው የባንክ አካውንት መላክ ይችላሉ፣ ኤምባሲው ደረሰኝ የሚልክ ይሆናል፣

**የባንክ አካውንቶች፡**

| የገንዘብ አይነት | የአካውንት ቁጥር | የድጋፍ አይነት |
|---|---|---|
| በአሜሪካ ዶላር | 1000001072475 | ቦንድ ግዥ |
| በዩሮ | 1000001040344 | ቦንድ ግዥ |
| በእንግሊዝ ፓውንድ | 1000001044943 | ቦንድ ግዥ |
| የአራቱም አገራት ገንዘብ (SEK, NOK, DKK, EURO) | Bank: Skandinaviska Enskilda Banken<br>Swift Code: ESSESESS<br>Account No: 52771122790<br>Account No: SE1150000000052771122790 | ስጦታ |

የኢትዮጵያ ኤምባሲ

Birger Jarlsgatan 39
111 45, Stockholm
P.O.Box 10148, SE-100 55 Stockholm
Email: ethemb.all@telia.com
Tel: +46-8-12048500 Fax: +46-8-6609561/8-6608177
Website: WWW.ethemb.se